# ሠ ቅ ዷ ሴ

**የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ልሣን**

Amara Survival for Ethiopian Unity Organization (ASEUO)

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!

| ልዩ | ዕትም፪፫ | ቀን: | ሰኔ ፱ | በየ15ቱ ቀን ዘወትር ኀሙስ የሚወጣ |
|---|---|---|---|---|


## መጠነኛ የጥገና ለውጥ ያስደነበረው የትግሬ-ወያኔ የመልሶ ማጥቃት አዋጅ አወጀ!

የትግሬ-ወያኔ ለሦስት ቀን መቀሌ ውስጥ መሽጎ በደረሰበት ስምምነትና በያዘው አቋም፣ በባድሜ ላይ የወሰደውን አቋሙን መልሶ ቀልብሶታል። እንደ መለስ “መሬቱን እንሰጣለን፤ ግን አፈጻጸሙ ላይ እንወያያለን” ወደሚለው የውኃ ቅዳ ውኃ መልስ አዙሪት መልሶታል። ከዚያም አልፎ ከትግሬ-ወያኔ ይፋ ዘረፋ በስም ብቻ የተረፉትን የሀገር ንብረቶች እንደተቋም ደግሞ የአገሪቱ ቢሮክራሲ ሞዴሎች ሆነው የሚታዩትን ወደ ግል ማዛወር በሚል ሽፋን ጠቅሎ ሊወስዳቸው የሚችልበትን መንገድ አስልቶ በእጁ ሊያስገባ በሚያስችለው ስልት ላይ ተስማምቷል።

ከዚህ እንደ ውሻ ወደ ትፋቱ የመመለስ አባዜ የተጠናወተው ይህ አገር አጥፊ ቡድን፣ የተፋውን መልሶ የላሰበትን የባድመ ጉዳይ፣ በተለይም በስፋት እያነጋገረ ያለውን በኦሕዴድ የበላይነት በመካሄድ ላይ ባለው መጠነኛ የጥገና ለውጥ በወያኔ ሠፈር ያሳደረው ሥጋትና ጭንቀት ከፍተኛ በመሆኑን በሚያሳብቅ መልኩ፣ ይህን መጠነኛ የጥገናዊ ለውጥ ለመቀልበስ የለቀቀው የመልሶ ማጥቃት እወጃ የትግሬ-ወያኔ አጥፍቶ ለመጥፋት ዝግጁ መሆኑን ያሳየ ነው። የትግሬ-ወያኔን ፍፁም የሆነ የበላይነትን በመጠኑም ቢሆን የተግደራደረውን የኦሕዴድን እርምጃ ቀይ መስመሩን ያለፈ የከሕደት ተግባር አድርጎ እንደቆጠረው የትግሬ ወያኔዎቹ የሦስት ቀን ስብሰባ መደምደሚያ የአቋም መግለጫ ቁልጭ አድርጎ አሳይቷል። ይህ የአቋም መግለጫ ከእንግዲህ በኋላ በኢሕአዴግ ውስጥ፣ በተለይም ደግሞ በትግሬ ወያኔና በኦሕዴድ መሀል የለየለት ትግል መጀመሩን ያበሰረ እወጃ መሆኑ ግልጥ ነው። የትግሬ ወያኔ ይህቺን በጣም የተመጠነች የኦሕዴድን የጥገና ለውጥ መሸከም እንኳን አለመቻሉን በሚገባ ያሳየበት እወጃ ነው።

የትግሬ ወያኔ ቢያውቅበትና ትንሽ ሆደ ሠፊነት ቢኖረው፣ የኦሕዴድ የተመጠነ የጥገና ለውጥ፣ አንገቱ ውስጥ ከተጠለቀለት ማነቆ የሚያላቅቀው አጋጣሚ መሆኑን ይረዳ ነበር። ግን የትግሬ ወያኔ በዘረፈው የሀብት ክምችት የደለበ፣ ጠቅሎ በያዘው ሥልጣን ማን አለብኝ በሚል የተወጠረ በመሆኑ ለራሱ መድኅንና መውጫ ቀዳዳ የከፈተለትን የኦሕዴድ የጥገና ለውጥ ለመቀበል አልተዘጋጀም። የትግሬ ወያኔ፣ በሕይወትም ውስጥ መሸነፍም እንዳለ የመገንዘብ ኅሊናውን የጥጋብ እና የእብሪት ሞራ ሸፍኖበታል። እናም ትዕቢቱን ማን አህሎኝ ባይነቱ ወደ ውድቀቱ በፍጥነት እየተጓዘ መሆኑ የወሰዳቸው አቋሞቹ በግልጽ ያሳያሉ።

ይህ የወያኔ ትግሬ የመልሶ ማጥቃት አዋጅ መሠረቱና ግቡ ምን እንደሆነ ለመረዳት፣ የአገሪቱን ወቅታዊ የኃይል አሰላለፎች መመልከት ተገቢ ነው። ማንም በግልጽ እንደሚረዳው፣ ኢሕአዴግን የትግሬ ወያኔ ነው የመሠረተው። ዓላማውም መሠረታዊ

ጠላቴ ያለውን ዐማራውን ለማጥፋት ነው። ይህም በመሆኑ ኢሕአዴግ በሚባለው የትግሬ ወያኔ ጭምብል በሚመራው መንግሥት ተብየ ባለፉት 28 ዓመታት ወደ 5ሚሊዮን የሚሆን ዐማራን በማጥፋት የፋሺሽትነት ድሉን ተጎናጽፏል። ይህም ሆኖ ግን፣ ዐማራውን ጨርሶ አላጠፋውም። እንዳውም ቀብረነዋል ካለበት መቃብሩ አፈሩንና ትቢያዉን አራግፎ ተደራጅቶ መነሳቱ ብርክ አስይዞታል።

ሌላው የኢሕአዴግ መመሥረት ዓላማ ኢትዮጵያ ከውስጥ ተበትናና ደክማ ለትግሬ-ወያኔ ወተት አቅራቢ ጥገት እንድትሆን ማስቻል ነው። ይህም ከጠበቀው በላይ ተሳክቶለታል። ከሦስት ዓመታት ቀደም ብሎ የተጀመረው ሕዝባዊ ትግል ይህን ጣምራ መመሪያውን ሽባ እንዲሆን አድርጎታል። በዚህ የሕዝብ ትግል ግፊት ተጠልሎ የተነሳው ኢሕአዴግ «እህት እና አጋር ድርጅቶች» በሚላቸው መካከል የእኩልነት እንቅስቃሴ መጎልበት ደግሞ የትግሬ ወያኔ ያልተጠበቀው ዱብ ዕዳን እንዲሸከም አድርጎታል።

ዛሬ በኢሕአዴግ ውስጥ የተነሳው የውስጥ ክፍፍል የሚከተለውን ይመስላል።

1 **በትግሬ ወያኔ ውስጥ የተነሳ ክፍፍል፡-** ክፍፍሉ ምንጊዜም በተሸናፊ ድርጅት ውስጥ እንደሚነሳ ክፍፍል ሁሉ፣ በወያኔም ውስጥ የተነሳው የመወነጃጀልና የመከዳዳት ባሕሪን ያስተናገደ መሆኑ የሚታይ ነው። በመሆኑም የገጠመውን የማይቀር ውድቀት ለመቋቋም የተሰባሰበ ሀሳብ አፍላቂ አመራር የለውም። የሚከተላቸውና የሚያወጣቸው ውሳኔዎች የሚጋጩና ተግባራዊ ሊሆኑ የማይችሉ ናቸው። ይህም በመሆኑ ድርጅቱን ይበልጥ ለጥቃት የሚያጋልጡት ይሆናሉ። የድርጅቱ ውድቀት እየፈጠነ ሲጓዝ፣ የትግሬ-ወያኔ እንደገና ወደ የማያልቅ ስብሰባ እንግባ ማለቱ የሚጠበቅ ነው። ለዚህም ነው ሌላ ስብሰባ እንዲደረግ ይኸኛው ስብሰባ ሀሳብ ያቀረበው። በዚህ ምክንያት የትግሬ-ወያኔ፣ እንኳን የፈጠረውን ኢሕአዴግን ሊመራ ቀርቶ፣ የትግሬ ነፃ አውጭ ቡድንን ሊመራ የማይችልበት ደረጃ ላይ ባጭር ጊዜ ውስጥ መውደቁ የማይቀር ነው።

2 **ኦሕዴድ ውስጥ ያለ ትግል፡-** ኦሕዴድ የራሱን ማንነት ካገኘ ገና ዓመት አልሞላውም። ፈጣሪው መለስ እንዳለው “እንደ ፈጣን ሎተሪ ሲፋቅ ኦነግ” ነው የተባለ ድርጅት ነበር። ዛሬም ኦነግ የተባሉት፣ አፍቃሪ የትግሬ ወያኔና ጠጋኝ ኃይሎች ተዳብለው የሚኖሩበት ድርጅት ነው። ከዚህ የተቃራኒ ስብስብ ውስጥ የነበሩት የነለማ ቡድን በተነሳው የሕዝብ ትግል በኢትዮጵያ ማዕቀፍ ውስጥ እንወክለዋለን ለሚሉት ማኅበረሳብ የሚበጅ ለውጥ ለማምጣትና ኢሕአዴግንም ለመለወጥ የተነሱ የጥገና ለውጥ አራማጆቹ መሆናቸው ነው ። የትግሬ ወያኔ ሕመም ከዚህ ላይ ይጀምራል። ይሁንና ዛሬም በድርጅቱ ውስጥ ኦነጎችና የኦነግ አፍቃሪዎች መኖራቸው ያደባባይ ሚስጢር ነው። ለነዚህ በኦህዴድ ውስጥ ላሉት የኦነግ አባላት መስራቾቹና ያለውን ህገመንግስት ያረቀቁ የነሌንጮ ለታ ወደ ሀገር መግባት ተጨማሪ ጉልበት እንደሰጣቸው የታወቀ ነው። ዛሬ በኦሮሚያ በሚባለው ውስጥ በጥገና ለውጥ አራማጆችና በኦነጎች መሀል የሚካሄደው የትግል መገለጫው በ”ክልሉ” ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለው ያለመረጋጋት ምክንያቱ ከዚያ ነው። በረጅም ጊዜ ጥቅም አንፃር በትግሬ ወያኔና በኦነግ መሀል የጠበቀ ግኑኘነት ይኖራል። ሁለቱም የደከመች ኢትዮጵያ ለግንጠላ ተግባራቸው አመቺ ናትና! ይህ አቋማቸው በኦሕዴድ ውስጥ ካሉትና በኢትዮጵያ ማዕቀፍ ውስጥ የጥገና ለውጥ አራማጆች ጋር ተፃራሪ ነው። ስለሆነም በነዚህ ኃይሎች መካከል የሚደረገው ትግል ይቀጥላል። የወያኔም የመልሶ ማጥቃት ጥሪ በነዚህ ተቀናቃኝ ኃይሎች መሀል ሚናን የሚያስለይ መሆኑ መያዝ አለበት።

3 **በብአዴን መሀል ያለ ትግል፡-** ብአዴን ከኦሕዴድም በከፋ መልኩ፣ ኅብረ ብሔርነት ነበር ይባልበት ከነበረው ኢሕዴን ወደ ብሔር ድርጅትነት ባንድ ሌሊት ተለውጦ፣ የዐማራውን ሕዝብ ለእልቂት ያዘጋጀው ዘንድ የተዋቀረ መሆኑ ይታወቃል። ድርጅቱ የትግሬ ወያኔን ዓላማ በዐማራው ማኅበረሰብ ዘንድ ለማስፈጸም የትግሬ ወያኔ የተደራጀና የተመራ ተላላኪ ድርጅት ነው። በመሆኑም ኦሕዴድ ዛሬ የኦሮሞን ሕዝብ ጥቅም ለማስቀደም የሚጫወተውንም ያህል ሚና የሚጫወት ድርጅት አይደለም። ይሁንና በዚህ የዐማራ ትግል መነሳሳት የተገፉና በደሉ የተሰማቸው ተራ አባላትና ዝቅተኛ የአመራር አባላት ከፍተኛ የሆነ መነሳሳት መፍጠራቸው የሚታይ ነው። በመሆኑም የነዚህ ኃይሎች ግፊት ተጠናክሮ በላይኛው አድርባይ አመራርና አፍቃሪ የትግሬ ወያኔ ባንዶች ላይ ሥጋት ሁኗል። ይህ ትግል በለውጥ ፈላጊው ኃይል ድል እንደሚደመደም ለትግሬ ወያኔ ግልጥ የሥጋት ምንጭ ሁኗል።

4 **የደቡብ ሕዝቦች ግንባር መሀል ያለ ትግል፡-** ይህ ድርጅት በባንዳው ፀረ ዐማራ በሽፈራው ሽጉጤ የሚመራ ድርጅት ነው። ድርጅቱ መሀል ክፍፍል እንዳለ በግልፕ የወጣው በአብይ ምርጫ ላይ ነው። ይህ መከፋፈል ዛሬም እንደ ዘለቀ የሚታየው በግልጽ በሕዝቡ በመነሳት ላይ ያለው የፀረ ሽፈራው ሽጉጤ አመራር ተጠናክሮ መቀጠል ነው። ይህንን ተቃውሞ የሚመራ የውስጥ ኃይል መኖሩን የሚጠቁም ትግል ነው በመካሄድ ላይ ያለው። ዛሬ በዚህ "ክልል" በወልቂጤ፣ በሻሸመኔ፣ በአርባምንጭና በሌሎችም ቦታዎች የሚታዩ በሽፈራው ሽጉጤ አመራር ደጋፊዎችና በጠቅላይ ሚኒስትሩ የጥገና ለውጥ ደግፊዎች መሀል የሚደረግ ትግል በይፋ ከአደባባይ ላይ ወጥቷል።

5 **በሶማሌ ድርጂት ውስጥ ያለ ትግል፡-** አብዲ ኢሌ በግልጽ ከትግሬ ወያኔ ጋር መወገኑ የታወቀ ነው። የመጨረሻ የመገንጠል ምኞታቸውም አንድ ነው። በግልጽ በጦር የኦሕዴድን አማራር እየወጋ መሆኑ የሚታይ ነው። ከአንድ ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ያፈናቀለ ባንዳ ነው። ዛሬ ይህንን የፀረ-ኢትዮጵያ መመሪያውን የሚቃወሙ የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎችና የአገር ሽማግሌዎች አዲስ አበባ ድረስ መጥተው ከአብይ ጋር ለመነጋጋር ሙከራ ቢያደርጉም ዕድሉን ተነፍገዋል። አብይ የወያኔን መልስ በመፍራት ነው ዕድሉን ያልሰጣቸው። ዛሬ ከፊሉን አቤት ባዮችን የወያኔና የአብዲ ኢሌ ሰላዮች አፍነው እንደወሰዷቸው ተሰምቷል። ሕዝቡም በሁሉም የሱማሌ አካባቢ የተቃውሞ ሰልፉን ከማድረግ አላቋረጠም። ይህ ትግልም መቋጫው በሕዝቡ አሸናፊነት መደምደሙ አይቀሬ ነው።

6 **በአፋር ድርጂት ውስጥ፡-** በአፋር ድርጅትም ውስጥ ያለው ትግል በአፍቃሪ ወያኔ ባንዶችና ቅድሚያ ለአፋር ሕዝብ በሚሉ፣ የትግሬ ወያኔን የግዛት መስፋፋት በሚቃወሙና በአፋር ወስጥ የትግራይን የኢኮኖሚ የበላይነትን በተለይም የጨውና የፖታሽ ምርትን የትግሬ ወያኔ ሞኖፖልን በሚቃወም ኃይል መካከል ያለው ቅራኔ ወደ አደባባይ ወጥቷል። ፍቺው በአፋር ሕዝብ ድል ማድረግ መደምደሙ አይቀሬ ነው።

በጠቅላላው በሀገሪቱ ዙሪያ የተቀጣጠሉ የፀረ የትግሬ ወያኔ ትግሎች ወያኔ የዘረጋውን የአገዛዝ የጭቆና መረብ እየቆራረጡት ነው። ሀገሪቱ ወደ አደገኛ የሥርዓት አልበኝነት ሕይዎት ውስጥ በመግባት ላይ እንዳለች ቁልጭ ብሎ እየታየነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሁነን ነው የትግሬ ወያኔ ሐርነት ትግራይ የመልሶ ማጥቃት እወጃውን የሰማነው።

እወጃው ምን ይላል?

፩. እወጃዉ የባድሜን ይዞታ መለስ ዜናዊ ወደ አወጣዉ ቅድሚያ እንደራደር መመሪያ መልሶታል፣

፪. በኦሕዴድ ማዕከላዊነት የሚካሄደውን ያልትጠበቀ ሹመትና ሽረትን እንደማይቀበል አሳውቋል፣

፫. የጠቅላይ ሚኒስትሩ አመራር ብቃት የሌለውና ከኢሕአዴግ የተለመደ የማዕከላዊነት አሠራር ያፈነገጠ ነው ይላል፣

፬. በሕገ መንግሥቱ የታወቁትን የማንነትና የግዛት ክፍፍልን ለማናጋት የተጀመረውን ትግል ከትግራይ ሕዝብ ጋር ሁነን እንዋጋለን በማለት ጦርነት አውጀዋል።

፭ ሕወሓትንና የትግራይን ሕዝብ ጥቅምንና ማንነትን ለመጋፋት በመሴር ላይ እንዳለና ይህንን ከትግራይ ሕዝብ ጋር ሁኖ ተዋግቶ እንደሚረታ ይፎክራል፣

፮. በአባል ድርጅቶች መካከል የገባውን የፀረ ኢሕአዴግ አዝማሚያን ለማጥራት የተስማማንበት ጉዳይ በሌሎች ስላልተገበረ ባስቸኳይ የፀረ ወያኔ ትግራይ ኃይሎች ከየድርጅቶቹ ተመንጥረው እንዲወጡ እንዲደረግ ይጠይቃል

፯. የትግሬ ወያኔዉ የአቋም መግለጫ፣ በኤርትራና በትግራይ ድንበር መሀል ላሉ ሕዝቦችና ለሚሊሻዎቹ ልዩ ባጀት እንዲመደብ ይጠይቃል። ጥያቄው በተዘዋዋሪ ዐማራው ጋር የሚጠብቀኝ ጦርነት ስለአለ "ክተት" ብሎ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሚሊሻ እንዲደራጅ ለያዘው የሥልጠናና የስምሪት ፕሮግራሙ የወረራ በጀት እንዲመደብለት መጠየቁ ነው፣

፰. ለአንጋፋ መሪዎቹ ዕውቅና እንዲሰጥ በሚል መመሪያ ሰጥቷል። ይህ ማለት ቢዘረዘር በጡረታ የወጡት በዐማራው ሕዝብ ላይ በፈጸሙት ወንጀል በሕግ እንዳይጠየቁ፣ የዘረፉት ገንዘብ እንዳይነካ፣ ከመንግሥት የሚያገኙት የነፃ ቤት፣ የመኪና አገልግሎት፣ የደምወዝ ክፍያ እንዳይቋረጥና በነፃነት እንዲዘዋወሩና ነግደው እንዲኖሩ መብታቸው እንዲጠበቅ ማለት ነው፣

፱. እነዚህ ከላይ የተገለጡት መመሪያዎችና የጦርነት እወጃዎች እንዳሉ ሁነው፣ በተጨማሪ የጠቅላይ ሚኒስትር አብይን ታማኝነት በሚጠይቅ መልኩ የሀገሪቱን ሁኔታና የአመራር አካሄዱን እንደገና ለመፈተሽ እንዲቻል አስቸኳይ የሆነ የኢሕአዴግ ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ እንዲጠራ ተዛዝ አስተላልፏል።

ይህ ጥሪ  ምን ማለት ነው? ጥሪው፣ በኦሕዴድና በወያኔ ትግራይ መካከል የሚካሄደውን ትግል ወደ ጫፍ ያደረሰ ጥሪ ነው። በሁለቱ መካከል ግንባር ለግንባር፣ በደጋፊዎቻቸውም መካከል በደጀን ሁኖ በሚደረግ ትግል አንዱ ሸብረክ ካለ ያልቅለታል። የሀገራችንንም የወደፊት ዕጣ ፈንታ የሚወስን ትግል መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። ኦሕዴድ ሸብረክ ብሎ እጁን ለትግሬ ወያኔ ከሰጠና ይቺን የጀመራትን የጥገና ለውጥ ጭራሹን ካዘገያትና ካጠፋት በተስፋ ሲያማልለው የነበር ሕዝብ ከሥሩ ያፈትልክና ለመሠረታዊ ለውጥ የሚደረገው የሕዝቡ ትግል በግልጽ ከአደባባይ ተመልሶ ይወጣል። ካሁን በኋላ በምንም ተአምር የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በተለይም የዐማራ ሕዝብ አንገቱን ለትግሬ ወያኔ ካራ ለመስጠት ቁጭ ብሎ አይቀመጥም።  እንደ ዐማራ ከናካቴው ላለመጥፋት ስንል የትግሬ ወያኔን በመጣበት አቅጣጫ ለመመከት እንሰለፋለን። በተቃራኒው ኦሕዴድና ደጋፊዎቹ የቆሙበትን ቦታ ይዘው የትግሬ ወያኔን ካገዱትና የሚመጣውን ለመቀበል ከቆሙ ሕዝቡ ይበልጥ ከጎናቸው በመቆም ወያኔን ይጋፈጣል። ይህም ሁኔታ ለኦሕዴድ አንድና አንድ ምርጫ ብቻ ነው የሚተውለት። የጥገና ለውጡን እርግፍ አድርጎ በመተው ለተቃዋሚ ኃይሎች ሁሉ እጁን መዘርጋትና ለመሠረታዊ ለውጥ በጋራ  መቆም!!  ከዚህ የተለየ አማራጭ መከተል ኦሕዴድ በራስ ላይ ሸምቀቆ ማጥበቅ ከመሆን የዘለለ አይሆንም።

**ማጠቃለያ፡-**  የትግሬ ወያኔ በአሁኗ ኢትዮጵያ ተገፍቶ ጥግ የያዘ፣ ምን ማድረግ እንዳለበት ለመለየት የተቸገረ፣ ግራ የተጋባ ኃይል ሆኗል ።  ሲጀመር ጀምሮ ጀብደኛና እብሪተኛ ድርጅት በመሆኑ፣ ግራ ቀኙን አይቶና ማምለጫ መንገድ የመፈለግና የመለሳለስ ባሕሪ የሌለው  ድርጅት በመሆኑ አጥፍቶ ለመጥፋት የማይፈነቅለው ደንጋይ ይኖራል ተብሎ አይታሰብም። ለዚህ አቋሙ ከፍተኛ ሚናውን የሚጫወተው በዐማራ ላይ ያለው ወደር የለሽ ጥላቻና የጠላትነት አቋሙ ነው። ከዐማራ ጋር በዕኩል/በጋር ሰፊ ቤት ውስጥ አብሬ አልኖርም ብሎ አስቀድሞ ገና ድሮ ወስኗል። ከዚህ ውሳኔው ማፈግፈግ ማለት ታሪካዊና ታሪክ ተሻጋሪ ሽንፈትን መቀበል አድርጎ የተቀበለ ድርጅት ነው። በመሆኑም የመጨረሻ ጦርነቱን በኃይል በወረረዉ ወልቃይት ጠገዴ፣ ራያና አካባቢዉ ላይ ቢያደርግ መደነቅ የለብንም። ዐማራም ለነባር ርስቱ እጁን አይስጥምና ትግሉ መቀጠሉ የግድ ነዉ። ይህንን ሐቅ ከግንዛቤ ውስጥ አስገብተን ካልተዘጋጀን ዐማራ እንደ ዐማራ ያልቅለታል።

ዐማራውን ለማጥፋት ከሚያደርገው የመጨራሻ ትግሉ ጎን ለጎን፣ ዛሬ በኢሕአዴግና በተባባሪ ድርጅቶች ውስጥ ባሉት ተላላኪዎች/ባንዶች አማካኝነት በማካሄድ ላይ ያለውን ሽብር የመፍጠርና አለመረጋጋትን በቅንጅት ማካሄዱን ይቀጥላል።  መመሪያው “እኔ ካልበላሁት ጭሬ እበትነዋለሁ” የሚለው አመሉ የታወቀ ነዉና።  ከዚህ አለማራጋጋት ጎን ለጎን፣ የተለመደ ስርቆትና ዘረፋው ይበልጥ ይካሄዳል።  የሀገሪቱ የጦር መሣሪያዎች ሁሉ ከመቸውም በባሰ መልኩ ትግራይ ውስጥ እንዲከማቹ እያደረገ ነዉ። እህል አስቀድሞ በምድር ዉስጥ ባዘጋጃቸዉ ዘመናዊ ጎተራዎች ሰብስቧል/እየሰበሰበም ነዉ።  በኦሕዴድና በደጋፊዎቹ ላይ ድል ከተቀዳጀ፣ የሕዝቡንና በተለይም የትግራይን ሕዝብ ተቃውሞ ለማወናበድ በሚል ከኤርትራ ጋር መለስተኛ የሚባል ግጪት ሊፈጥር እንደሚችልም ታሳቢ ማድረግ መልካም ነው። ይህ ሁሉ ሁኖ የትግሬ ወያኔ ሤራ ለመበጣጠስ የሚረዳው ባጭር ጊዜ የኦሕዴድንና ደጋፊ ድርጅቶችን ትግል መደገፉ ለጥገና ለውጥ አራማጆች ብቻ ሳይሆን ለኛ ለመሠረታዊ ለውጥ አራማጆቹም ተገቢ ነው። ምንም ዓይነት ትግል የትግሬ ወያኔን እስካዳከመና ወደ መውደቂያው እስከ ወሰደው ጊዜ ድረስ  ለመሠረታዊ ለውጥ ጉዟችን ስንቅ ነው።  በመሆኑም፣ ባሁኑ ትግል ከፀረ ወያኔ ግንባር ጎን ቁመን የድሉ ተካፋይ ልንሆን ይገባል። ኦሕዴድም ምርጫው እጁን ሰጥቶ ወደ ቀድሞው ባርነቱ መመለስ ወይም ደግሞ ከመሠረታዊ ለውጥ አራማጅ ኃይሎች ጎራ በመግባት የሕዝቡን የመሠረታዊ ለውጥ ጥያቄን ተግባራዊ ማድረግ ለድርጅቱ እንደ ድርጅት፣ ለኦሮሞ ሕዝብም እንደ ሕዝብ ኩራትና ክብርን የሚያጎናጽፍ መልካም ተግባር ይመስለናል። ይህ እጅግ በጣም የተለየ ታሪካዊ ምዕራፍ ነዉና ዶ/ር አብይ ሳይቀደም በቆራጥነትና በብቃት የለዉጥ ሂደቱን እየነጎደ ካለዉ ጊዜ ጋር በፍጥነት እንዲስኬደዉ የዐማራ ኅልዉና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) በጽኑ ያሳስባል። ይህ ሲሆን የኢትዮጵያን ሕዝብና የለዉጥ ኃይሎችን ሙሉ በሙሉ ድጋፍ ያገኛል --- ሌላ ሦስተኛ አማራጭ መንገድ የለምና!!

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ የኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

እናት ኢትዮጵያን እንታደጋት!!